Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

# ለመጀመሪያ ግምገማ/ምዘና የሚሰጥ ማሳወቂያ እና ፈቃድ

**ዓላማ:-** *የመጀመሪያ ግምገማ/ምዘና እንዲደረግ ሃሳብ የቀረበ እንደሆነ ለወላጅ በጽሁፍ ለማሳወቅ እና የመጀመሪያ ግምገማ/ምዘናውን ለማድረግ ከወላጅ ፈቃድ ለማግኘት።*

| የልጅ ሥም | የትውልድ ቀን | የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ |
|---|---|---|
| | | |

**ማሳወቂያው የተሰጠበት ምክንያት**

የ ESIT ፕሮግራም የግምገማ እና ምዘና ተግባራትን ከማከናወኑ በፊት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ እንዲሰጥዎ ይገደዳል። ለእነዚህ ተግባራት ከዚህ በታች በሚያሰፍሩት ፊርማዎ አማካኝነት በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ የጽሁፍ ፈቃድ እንዲሰጡ ያስፈልጋል። የግምገማ እና ምዘና ዓላማ ከእርስዎ እና እርስዎ እንዲሳተፉ ከሚጠይቋቸው ሌሎች ሰዎች ስለ ልጅዎ መረጃ ማግኘት፤ ስለልጅዎ ዕድገት ለቤተሰብዎ ተጨማሪ መረጃ መስጠት፤ የልጅዎን ልዩ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች መለየት እና እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት አግባብ ሊሆኑ የሚችሉ አገልግሎቶችን መለየት፤ ልጅዎ ለ ESIT ፕሮግራም ብቁ መሆኑን መወሰን፤ እና ልጅዎ ብቁ ከሆነ፤ በእርስዎ ስምምነት እና ተሳትፎ፣ በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) በጽሁፍ ማዘጋጀት ነው። ይህ ያንን ማሳወቂያ በተመለከተ ለእርስዎ የተሰጠ መግለጫ ነው

> *"ፈቃድ" ሰጥተዋል ማለት፦ (1)ፈቃድዎ ከተጠየቀባቸው ተግባራት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም መረጃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ (ይህንን ለማድረግ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ካልሆነ በስተቀር) ወይም እንደ አግባብነቱ የምልክት ቋንቋን፣ ብሬልን ወይም የቃላት ተግባቦትን ጨምሮ በሌላ የተግባቦት መንገድ ሙሉ በሙሉ ማግኘትዎን፤ (2) ፈቃድዎ ስለተጠየቀባቸው ተግባራት ተረድተው እነዚህን ለማከናወን በጽሁፍ ፈቃድ መስጠትዎን (3) ፈቃዱ የሚከናወኑትን ተግባራት እና ለሌሎች ሰዎች የሚሰጡትን ማህደሮች (ካሉ) ለማን እንደሚሰጡ ጨምሮ ይዘረዝራል፤ (4) ፈቃድዎን የሰጡሁት በፈቃደኝነት መሆኑን እና በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ በማሳወቅ ሊያነሱት እንደምችሉ መረዳትዎን። ፈቃድዎን ካነሱ፣ ወደ ኋላ የሚሰራ ላይሆን*ም (ማለትም፣ ፈቃዱ ከመነሳቱ በፊት ለተወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች አያገለግልም።)

**እንዲወሰድ የቀረበ እርምጃ**

ከሁለት የተለያዩ የስራ ዘርፎች በመጡ ቢያንስ ሁለት ብቃት ያላቸው ግለሰቦች (ወይም በሁለት ዘርፎች ብቃት ባለው አንድ ባለሙያ) በ ESIT ፕሮግራም ፖሊሲዎች እና ሥርዓቶች መሰረት ግምገማ እና ምዘና ይከናወናል። እንደ ግምገማው ቡድን አባልነት የእርስዎ ተሳትፎ በእጅጉ ይበረታታል። ልጅዎን በተሻለ ስለሚያውቁት ስለልጅዎ ወሳኝ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። ግምገማ እና ምዘናው ልጅዎ በአእምሮ፣ በአጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እንቅስቃሴ፣ በተግባቦት፣ በማህበራዊ-የስሜት እና ራስን የማላመድ ዕድገት፣ እንዲሁም በዕይታ እና በመስማት ምን ያህል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በተሟላ ሁኔታ መመልከት ነው። ውጤቶቹ ልጅዎ በሁሉም ዘርፎች ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እና የ ESIT አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ነው አይደለም የሚለውን ያመላክታሉ።

***መግለጫ***

የሚቀርበው ግምገማ በርካታ ቅደም ተከተሎችን የሚያካትት ሲሆን ከእነዚህም መካከል የግምገማ ሰነድን ማስተዳደር፣ የልጁን ታሪክ መውሰድ፣ ወላጅ(ጆች)ን ማነጋገር፣ ከሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ከተንከባካቢዎች ወይም ከሌሎች የሕክምና ወይም ሌላ ሙያተኞች መረጃ መሰብሰብን እንዲሁም የሕክምና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማህደሮችን መመልከትን ያካትታል። የሚቀርቡት የምዘና ቅደም ተከተሎች የልጅዎን ልዩ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች እና አግባብ የሆኑ የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይወስናሉ። ምዘና የሚያካትተው፦-የግምገማ ውጤቶችን መከለስ፤ በልጁ ላይ የሚደረግ ግላዊ ምልከታ፣ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የምዘና ቅደም ተከተሎችን በመጠቀም በእያንዳንዱ የዕድገት ክልል ላይ የልጁን ፍላጎቶች መለየት። ለዚህ ግመግማ እና ምዘና የሚጠቀሟቸውን ዘዴዎች በተመለከተ የ ESIT አገልግሎት ሰጪዎች ከእርስዎ ጋር ይነጋገራሉ። ግምገማው እና ምዘናው እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ ይከናወናል። ውጤቶቹም በልጅዎ የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ ማህደር ውስጥ ይቀመጣል። እርስዎ ያንን ለማድረግ በጽሁፍ ፈቃድዎን ካልሰጡ በስተቀር የትኛውም መረጃ ከ ESIT ፕሮግራም ውጪ ላለ ማንኛውም ሰው ወይም ኤጀንሲ አይሰጥም። የ IFSP ቡድን ልጅዎ ብቁ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፣ እናም የብቁነት ውሳኔውን ለመቃወም ያለዎትን መብት ጨምሮ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጥዎታል።

***የጊዜ ሠሌዳዎች***

*ልጅዎ ወደ ESIT ፕሮግራም የተመራበት ቀን።*

ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች ከመጡ ሙያተኞች የተውጣጣው ይህ ቡድን ግምገማ/ምዘና ያከናውንና ልጅዎ ብቁ ከሆነ፣ እና እርስዎ ከተስማሙ፣ ልጅዎ ከተመራበት ቀን አንስቶ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) መጠናቀቅ አለበት። ቤተሰብዎ ከ45 ቀናቱ በላይ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ ከሆነ፣ ለቤተሰብ መረጃ አስተባባሪዎ መንገርዎ አስፈላጊ ነው። IFSP የልጅዎን እና የቤተሰብዎ ቀጣይ ፍላጎቶች ለማሟላት ከቤተሰብዎ እና ከሙያተኞች ጋር አጋር በመሆን በጽሁፍ የሚዘጋጅ ዕቅድ ነው። ይህ በማንኛውም ጊዜ ሊለወጥ ይችላል። IFSP የሚጻፈው ልጅዎ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ከሆነ ብቻ ነው።

*ማረጋገጫ እና የፈቃድ መግለጫ*

**ከዚህ ማሳወቂያ ጋር የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (*IDEA*) ክፍል ሐ የሥነ-ስርዓት**

*የወላጅ ፊርማ*

***ጥበቃዎችን [የወላጅ መብት]) ቅጂ ደርሶኛል።*** *እነዚህ መብቶች እና የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች ተብራርተውልኝ እኔም ተረድቻቸዋለሁ። ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የተሰጠ መሆኑን እና ይህን ቅጽ ከፈረምኩኝ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ልጄ እንዳይገመገም ማድረግ የምችል መሆኑን ተድቻለሁ። ለዚህ ግምገማ እና ምዘና ፈቃድ መስጠት ካልፈለግኩኝ፣ ልጄ እንደማይገመገም ወይም ምዘና እንደማይደረግለት እና በ ESIT ፕሮግራም ስር የሚሰጡ የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ አገልግሎቶችን ማግኘት እንደማይችል ተረድቻለሁ።*

| | | |
|---|---|---|
| ☐ **ፈቃዴን እሰጣለሁ** | ☐ **ፈቃዴን አልሰጥም** | የESIT ፕሮግራም ከላይ የተገለጹትን ተግባራት እንዲያከውን ወይም እንዳያከናውን በመረጃ ላይ የተመሰረ ፈቃድ |

| | |
|---|---|
| **የወላጅ(ጆች) ሥም** | |
| **የወላጅ(ጆች) ፊርማ** | **ቀን** |
| **የተቀበለው ሰው ስም/ማዕረግ/ኤጀንሲ** | **ቀን** |

*አባሪ፦ የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች[የወላጅ መብት])*
*ማስታወሻ፦ ወላጆች የዚህ ቅጽ ግልባጭ የሚደርሳቸው ሲሆን የተፈረበመት ቅጂ ደግሞ በልጁ የጨቅላነት ጊዜ አገልግሎት ማህደር ውስጥ ይካተታል።*